ሠላሳ አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፳
35th Year — No. 20

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.
Addis Ababa, 4th February, 1976

የኢትዮጵያ ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት

# ነጋሪት ፡ ጋዜጣ ።

# NEGARIT GAZETA

| የጋዜጣው ፡ ዋጋ ፤ | | በጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀ መንበር ጽሕፈት ቤት ተጠባባቂነት የወጣ | ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ይታተማል ። |
|---|---|---|---|
| ባገር ፡ ውስጥ ፡ ባመት ፡ | $ ፲ | | የፖስታ ሣጥን ቁጥር ፩ሺ፴፩ (1031) |
| » » በ፮ ፡ ወር ፡ | $ ፫ | | |
| » » ያንዱ ፡ | $ ½ | | |


ማውጫ
፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

አዋጅ ቁጥር ፸፰/፲፱፻፷፰ ዓ. ም.
የሕዝብ ማስፈር ባለሥልጣን ማቋቋሚያ
አዋጅ . . . . . . . . . . . . . ገጽ ፻፵፬

CONTENTS
1976

Proclamation No. 78 of 1976
Settlement Authority Establishment
Proclamation . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . Page 144

## አዋጅ ቁጥር ፸፰/፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

## የሕዝብ ማስፈር ባለሥልጣንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

« ኢትዮጵያ ትቅደም »

የሕዝብ ማስፈር ፕሮግራም የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣውን አዋጅ በሥራ ላይ እንዲውል ከመደገፉም ሌላ የገጠሪቱን የልማት እንቅስቃሴ ወደፊት እንደሚያራምደው የታመነበት ስለሆነና እንዲሁም በማንኛ ውም ድርጅት በሥራ ላይ ያልዋሉትን መሬቶች ለሰፊው ሕዝብ ጥቅም እንዲውሉ የሚያደርግ በመሆኑ ፤

የእርሻ መሬት በማነሱ ምክንያት ያለመሬት ለሚቀሩ ወይም ይዞታቸው እጅግ አነስተኛ የሆኑትን አራሾች በየከተማው ሥራ አጥተው የሚንከራተቱትን ለእርሻ ምቹ በሆኑ ቦታዎች ላይ ለማስፈር ፤

የአፈርና የውሃ እንዲሁም የደን ጥበቃ ፕሮግራሞችን በማስፋፋት ምክንያት ቦታዎችን የሚለቁ ሰዎችን ወደ ሌላ ቦታ ማስፈር አስፈላጊ ስለሚሆን ፤

ዘላኖች በይዞታቸው ላይ በዘመናዊ የከብት እርባታም ሆነ በእርሻ እንዲሰማሩ ማበረታታትና ማስፈር አስፈላጊ ስለሆነ ፤

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚካሄዱትን ልዩ ልዩ የሕዝብ ሠፈራ ፕሮግራሞች በማስተባበር ለሰፊው ሕዝብ ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጡና ለአገሪቷ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የሚረዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ አንድ ራሱን የቻለ መንግሥታዊ ድርጅት አስፈላጊ መሆኑን በማመን ፤

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀ መንበሩን ሥልጣን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፪/፲፱፻፷፯ ዓ.ም በአንቀጽ ፮ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል ።

## PROCLAMATION No. 78 OF 1976

## A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF A SETTLEMENT AUTHORITY

**"ETHIOPIA TIKDEM"**

WHEREAS, a settlement programme not only complements the implementation of the Public Ownership of Rural Lands Proclamation but is also believed to promote the economic development of the rural sector and to bring under use for the benefit of the broad masses those lands not utilized by any organization;

WHEREAS, it is necessary to settle those farmers who remain with very small or no rural holdings and the jobless in urban centres;

WHEREAS, it is necessary to resettle in other areas those persons whose holdings are reserved for the expansion of soil, water and forest conservation programmes;

WHEREAS, it is necessary to encourage nomads to develop their present holdings into modern pastoral and arable farming;

WHEREAS, it is necessary to establish an autonomous Government agency to make sure that all settlement programmes within the country are co-ordinated with a view to yielding maximum benefit to the broad masses and to supporting the protection of the natural resources of the country;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 6 of the Definition of Powers of the Provisional Military Administration Council and its Chairman Proclamation No. 2/1974, it is hereby proclaimed as follows:

**፩ ፤ አጭር ርእስ ፤**

ይህ አዋጅ « የሕዝብ ማስፈር ባለሥልጣን ማቋቋሚያ አዋጅ ቍጥር ፸፰/፲፱፻፷፰ ዓ. ም. » ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

**፪ ፤ ትርጓሜ ፤**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩/ « ሠፈራ » ማለት ሰዎች በእርሻ ወይም ከእርሻ ግንኙነት ባለው ሥራ ተሰማርተው እንዲኖሩ ለማድረግ የተፈጸመ ተግባር ነው ።

፪/ « ሠፋሪ » ማለት ባለሥልጣኑ ያሰፈረው ሰው ነው ።

**፫ ፤ የባለሥልጣኑ መቋቋም ፤**

ከዚህ ቀጥሎ « ባለሥልጣን » እየተባለ የሚጠራ የሕዝብ ማስፈር ባለሥልጣን ራሱን የቻለ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ።

**፬ ፤ ዓላማዎች ፤**

ባለሥልጣኑ ፤

፩/ መሬት ያነሳቸውን ወይም የሌላቸውን ሰዎች የማስፈር ፤

፪/ በልዩ ልዩ ምክንያት በጥቅም ላይ ያልዋሉትን መሬቶች በጥቅም ላይ እንዲውሉ የማድረግ ፤

፫/ የሀገሪቱን የሥራ እጥረት ችግር የማቃለል እና

፬/ አግባብ ካላቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የደን ፤ የአፈርና የውሃ ሀብቶች እንዳይባክኑ የማድረግ ፤

ዓላማዎች ይኖሩታል ።

**፭ ፤ የባለሥልጣኑ ችሎታ ፤**

ባለሥልጣኑ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ሆኖ ፤

፩/ የመክሰስና የመከሰስ ፤

፪/ ውል የመዋዋል ፤ ዕርዳታ የመቀበል ፤

፫/ ዓላማውን ከግብ ለማድረስና የሥራ አፈጻጸሙን ለማሳካት ፤ ንብረት የማግኘት ፤ የማበጀት ፤ የመያዝ ፤ የማስያዝና የመሸጥም ሆነ የመለወጥ ፤

፬/ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶችን የማቋቋም ፤

፭/ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልጉ ተግባሮችንና የሥራ ክንውኖችንና የመፈጸም ፤

ችሎታ ይኖረዋል ።

**፮ ፤ የባለሥልጣኑ ተግባርና ሥልጣን ፤**

ባለሥልጣኑ ፤

፩/ ለሠፈራ አመቺ የሆኑትን ቦታዎች በማጥናት መዝግቦ የመያዝ ፤

፪/ ለሠፈራ የሚያስፈልገውን ጠቅላላ መመሪያ አያዘጋጂ በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ፤

፫/ ሰዎችን የማስፈር ፤

፬/ በመንግሥትም ሆነ በግል ድርጅቶች የሚካሄዱትን ልዩ ልዩ የሕዝብ ሠፈራ ፕሮግራሞችን የማስተባበር፤ የመቆጣጠርና አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ ተረክቦ የማካሄድ ፤

፭/ የረጅምና የአጭር ጊዜ ሠፈራ ፕሮግራሞችን የማዘጋጀት ፤

፮/ የሠፋሪዎችን የስም ዝርዝር ከበቂ መለያ ምልክቶቻቸው ጋር መዝግቦ የመያዝ እና ከሠፈራ ቦታ ለቀው የሚሄዱትን ሰዎች ዝርዝር ለፖሊስ የማስተላለፍ ፤ እና

1. *Short Ttitle*

This Proclamation may be cited as the "Settlement Authority Establishment Proclamation No. 78/1976".

2. *Definitions*

In this Proclamation, unless the context otherwise requires:

1/ "Settlement" shall mean the act of establishing people in agriculture or related activities;

2/ "Settler" shall mean any person whom the Authority settles.

4. *Establishment of the Authority*

There is hereby established a Settlement Authority, hereinafter called the "Authority" as an autonomous Public Authority.

4. *Objectives*

The objectives of the Authority shall be:

1/ the setlement of persons who have little or no land;

2/ the utilization of lands that remain idle for various reasons;

3/ the alleviation of the unemployment problems of the country; and

4/ the conservation of forest, soil and water resources in consultation with the appropriate Government agencies;

5. *Capacities of the Authority*

The authority shall have juridical personality with the capacity to:

1/ sue and be sued;

2/ enter into contract and accept aid;

3/ acquire, own, hold, mortgage, sell and exchange property to achieve its objectives and accomplish its tasks;

4/ establish branch offices; and

5/ carry on such other activities as are necessary for the achievement of the goals for which it is established.

6. *Powers and Duties of the Authority*

The Authority shall have the following powers and duties:

1/ to identify areas that are suitable for settlement and draw up an inventory thereof;

2/ to prepare a general land settlement policy and ensure the implementation of same;

3/ to settle people;

4/ to co-ordinate and supervise the various settlement programmes carried out by private or governmental organizations and to take over and operate them when necessary;

5/ to prepare short and long term settlement programmes;

6/ to register the settlers with their adequate identifications and to give to the police the list of names of those who abandon the settlement site; and

፯/ የሠፈራ ፕሮግራሞችን በሥራ ላይ ለማዋል የሚያስፈልጉትን ሌሎች ተግባሮች የመፈጸም ፤
ተግባርና ሥልጣን ይኖረዋል ።

**፯ ፤ የባለሥልጣኑ አቋም ፤**

ባለሥልጣኑ ፤

፩/ የሕዝብ ማስፈር ቦርድ (ከዚህ በኋላ « ቦርድ » ተብሎ የሚጠራ)

፪/ አንድ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤ አንድ ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅና

፫/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ፤

ይኖሩታል ።

**፰ ፤ የቦርዱ አባሎች ፤**

ቦርዱ የሚከተሉት ስባት አባሎች ይኖሩታል ፤

፩/ የመሬትና የሕዝብ ማስፈር ሚኒስትር - - ሊቀ መንበር
፪/ የእርሻና የደን ልማት ሚኒስትር - - ም/ ሊቀ መንበር
፫/ የአገር አስተዳደር ሚኒስትር - - - - አባል
፬/ የሠራተኛና የማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር - - - »
፭/ የፕላን ኮሚሽነር - - - - - - - - »
፮/ የእርዳታና ማቋቋሚያ ማስተባበሪያ ኮሚሽነር - - »
፯/ ዋና ሥራ አሥኪያጅ - - - - - - - »

**፱ ፤ የቦርዱ ሥልጣን ፤**

በዚህ አዋጅ ሌሎች አንቀጾች የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ የባለሥልጣኑ ተግባርና ሥልጣን የቦርዱ ናቸው ።

**፲ ፤ የቦርዱ ስብሰባ ፤**

፩/ ቦርዱ በወር አንድ ጊዜና የባለሥልጣኑ ሥራ ከንውን እንዳስፈለገ ከዚያም አጠር ባለ ጊዜ ይሰበሰባል ።

፪/ ከቦርዱ አባሎች አራቱ በስብሰባው ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል ። ቦርዱ ውሳኔውን የሚያሳልፈው በድምፅ ብልጫ ሲሆን ፤ ድምፁ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሊቀ መንበሩ ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል።

፫/ ቦርዱ በሊቀ መንበሩ ጥያቄ ወይም በቦርዱ የሥነ ሥርዓት ደንብ መሠረት ይሰበሰባል ።

፬/ ቦርዱ የራሱን የሥነ ሥርዓት ደንብ ያወጣል ።

**፲፩ ፤ ዋና ሥራ አስኪያጅ ፤**

፩/ ዋናው ሥራ አስኪያጅና ም/ ዋና ሥራ አስኪያጁ በቦርዱ አሳሳቢነት በመንግሥት ይሾማሉ ።

፪/ ዋናው ሥራ አስኪያጅ የባለሥልጣኑ የበላይ ሥራ አስፈጻሚ ሹም ሆኖ ከቦርድ በሚሰጠው ጠቅላላ መምሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች በኃላፊነት ያካሄዳል ፤

፫/ ከዚህ በላይ በአጠቃላይ የተመለከተው ሳይነካ ፤ ዋናው ሥራ አስኪያጅ የሚከተሉትን ያከናውናል ፤

ሀ/ በመንግሥት ሠራተኞች ማስተዳደሪያ ጠቅላይ መሥሪያ ቤትና የመንግሥትን ሠራተኞች ትእዛዝ ቁጥር ፳፫/፶፬ እና በሥሩ በወጡት ደንቦች መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያዛውራል ፤ ያሰናብታል ፤ ያስተዳድራል ፤

ለ/ የገንዘብ ወጭ ያደርጋል ፤

ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና ዝርዝር የዓመት በጀት አዘጋጅቶ ቦርዱ እንዲያጸድቀው ያቀርባል ፤

7/ to carry on other activities necessary for the accomplishment of its settlement programmes.

7. *Organization of the Authority*

The Authority shall have:

1/ a Settlement Board, hereinafter called the "Board";

2/ one General Manager and one Deputy General Manager; and

3/ the necessary personnel.

8. *Board Members*

The Board shall consist of the following members:

| | |
|---|---|
| 1/ the Minister of Lands and Settlement... | Chairman |
| 2/ the Minister of Agriculture and Forestry .. .. .. .. .. .. .. | Vice Chairman |
| 3/ the Minister of Interior .. .. .. | Member |
| 4/ the Minister of Labour and Social Affairs .. .. .. .. .. .. | " |
| 5/ the Commissioner of Planning . .. | " |
| 6/ the Commissioner of Relief and Rehabilitation .. .. .. .. .. | " |

9. *Powers of the Board*

Subject to the other provisions of this Proclamation, all the powers and duties of the Authority are vested in the Board.

10. *Meetings of the Board*

1/ The Board shall meet once a month and at shorter intervals as the work of the Authority may require.

2/ Four (4) members of the Board shall constitute the quorum. The Board shall make decisions by majority vote. In case of a tie, the Chairman shall have a casting vote.

3/ The Board shall meet upon the request of the Chairman or according to the rules of procedure of the Board.

4/ The Board shall adopt its own rules of procedure.

11. *The General Manager*

1/ The General Manager and Deputy General Manager of the Authority shall be appointed by the Government upon the recommendation of the Board.

2/ The General Manager shall be the chief executive officer of the Authority, and shall direct and supervise its operations and management subject to the general direction of the Board.

3/ Without limiting the generality of the foregoing the General Manager shall:

a) employ, transfer, dismiss and administer the personnel of the Authority in accordance with the Central Personnel Agency and Public Service Order No. 23/1961 and regulations issued thereunder;

b) incur expenditures;

c) draw up and submit to the Board for approval the Authority's work programme and detailed annual budget;

መ/በማንኛውም የሕግ ጉዳይ ባለሥልጣኑን ይወክላል ፤
ሠ/የባለሥልጣኑን የሥራ ክንውን የሚያሳይ ዓመታዊ ሪፖርት ያዘጋጃል ።

፬/ ዋናው ሥራ አስኪያጅ ለባለሥልጣኑ ሥራ አፈጻጸም አስፈላጊ በሆነ መጠን ከሥልጣኑ ለም/ዋና ሥራ አስኪያጁና ለባለሥልጣኑ ሹሞች ይሰጣል ።

**፲፪ ፤ በጀትና የበጀት ዓመት ፤**

፩/ ባለሥልጣኑ ከመንግሥት በሚያገኘው በጀት ይተዳደራል ።
፪/ ባለሥልጣኑ የዓመት የሂሳብ መግለጫዎች የበጀት ዓመት ባለቀ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ለገንዘብ ሚኒስቴርና ለጠቅላይ ኦዲተር መሥሪያ ቤት ያቀርባል ።
፫/ የባለሥልጣኑ የበጀት ዓመት ሐምሌ ፩ ቀን ጀምሮ ሰኔ ፴ ቀን ያልቃል ።

**፲፫ ፤ በሠፈራ ፕሮግራም ለመጠቀም የሚያስችሉ ሁኔታዎች**

በሠፈራ ፕሮግራም የሚጠቀሙ ፤
፩/ በዕድሜ ፤ በጤንነትና ፤ በዝንባሌ በፕሮግራሙ ሊሳተፉ ይችላሉ ብሎ ባለሥልጣኑ የሚገምታቸው እና
/ ፪ ( [illegible] የቀሩ ወይም ይዞታቸው አነስተኛ የሆነ አራሾች ወይም ፤
፫/ በየከተማው በሥራ እጦት የሚገኙ ሰዎች ወይም
፬/ በአርሻ ሥራ ተሰማርተው ለመኖር የሚፈልጉ ዘላኖች ወይም ፤
፭/ በሌሎች በልዩ ልዩ ምክንያት መስፈር የሚያስፈልጋቸው
ሰዎች ናቸው ።

**፲፬ ፤ የቅድሚያ መብት ፤**

ለሠፈራ በተመረጠው አካባቢ የሚኖሩት ሕዝቦች ለመስፈር ቅድሚያ ይኖራቸዋል ።

**፲፭ ፤ ለሠፋሪ የሚሰጥ ይዞታ መጠን ፤**

የገጠርን መሬት የሕዝብ ሀብት ለማድረግ የወጣውን አዋጅ ቁጥር ፴፩/፲፱፻፷፯ መሠረት በማድረግ ለመተዳደሪያ የሚበቃ መሬት ለያንዳንዱ ሠፋሪ በይዞታ ይሰጣል ።

**፲፮ ፤ ሠፈራ የሚፈጸምባቸው መሬቶች ፤**

ሠፈራ የሚፈጸምባቸው መሬቶች ፤
፩/ በማናቸውም ሰው ወይም ድርጅት ያልተያዙ ወይም በጥቅም ላይ ያልዋሉ እና
፪/ ባለሥልጣኑ ለሠፈራ ቢውሉ የበለጠ የኤኮኖሚና የሶሺያል ውጤት ያስገኛሉ ብሎ የሚያቀርባቸውና መንግሥት የሚስማማባቸው ፤
ይሆናሉ ።

**፲፯ ፤ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ግዴታ ፤**

ማናቸውም የመንግሥት መሥሪያ ቤት ሠፈራን በሚመለከት ረገድ ከባለሥልጣኑ ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት ።

**፲፰ ፤ ቅጣት ፤**

ይህን አዋጅ የጣሰ ወይም በአዋጁ መሠረት የተሰጠውን ትእዛዝ ያላከበረ ማናቸውም ሰው ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ይቀጣል ።

d) represent the Authority in all legal matters;
e) prepare an annual work report of the Authority.

4/ The General Manager shall, to the extent necessary for the efficient administration of the Authority, delegate his powers to the Deputy General Manager and other officers of the Authority.

12. *Budget and Fiscal Year*

1/ The Authority shall function with a budget allotted by the Government.
2/ The Authority shall submit its financial statement to the Ministry of Finance and the Auditor General's Office within three months from the end of each fiscal year.
3/ The fiscal year of the Authority shall begin on the 1st day of Hamle and end on the 30th day of Sene.

13. *Settler Criteria*

The beneficiaries of the settlement programme shall be:
1/ persons whom the Authority deems capable of participating in the programme after consideration of their age, health and interest, and
2/ persons with small or no land, or
3/ unemployed persons who reside in urban areas, or
4/ nomads desirous of being settled, or
5/ persons who need to be settled for various other reasons.

14. *Right of Priority*

Priority of settlement shall be given to persons residing in the general vicinity of the settlement site.

15. *Size of Holding to be Allotted per Settler*

A settler shall be allotted land sufficient for his maintenance, in accordance with the Public Ownership of Rural Lands Proclamation No. 31/1975.

16. *Lands for Settlement*

Settlement shall be undertaken:
1/ on lands unoccupied or not utilized by any person or organization and
2/ with the consent of the Government, on lands which the Authority considers will give better economic and social results.

17. *Obligations of Public Authorities*

All Public Authorities shall co-operate with the Authority in matters relating to settlement.

18. *Penalty*

Any person who violates this Proclamation or disobeys the orders issued hereunder shall be punishable with imprisonment not exceeding one year.

፲፱ ። ደንብ የማውጣት ሥልጣን ።

የቦርዱ ሊቀ መንበር በቦርዱ አሳሳቢነት ይህን አዋጅ በሚገባ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ያወጣል ።

፳ ። አዋጁ የሚጸናበት ቀን ።

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ።

አዲስ አበባ ጥር ፳፯ ቀን ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.

ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ

19. *Power to Issue Regulations*

The Chairman of the Board shall, upon the recommendation of the Board, issue regulations for the proper implementation of this Proclamation.

20. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force on the date of its publication in the Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 4th day of February, 1976

*THE PROVISIONAL MILITARY ADMINISTRATION COUNCIL*